# የየም ልዩ ወረዳ የአቅም ግንባታ ጽ/ቤት የአመቱ ማጠቃለያ ሪፖርት

3.1 ቁልፍ ውጤቶች

1. የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ የሙሉ ትግበራ በተመለከተ፡-

3. የታቀዱ ተግባራት

3.1 የታቀዱ ቁልፍ ተግባራት

3.1.3. መሰረታዊ የሥራ ሂደት ጥናት ትግበራ ያደረጉ 6(ስድስት) መ/ቤቶች፣ 2(ሁለት) ማዘጋጃ ቤቶች፣ እና 9(ዘጠኝ) ሌሎች መ/ቤቶች፤

የታቀዱ ዝርዝር ቁልፍ ተግባራት

3.1.1.1. በእያንዳንዱ ሴክተር ወደ ሙሉ ትግበራ ከመግባቱ በፊት ስለተከናወኑ ተግባራት፤

3.1.1.2. የእያንዳንዱ የስራ ሂደት ባለቤትና ፈፃሚዎች አመዳደብ፣ የአሠራር አተገባበር፤

3.1.1.3. ስለ ለውጥ ተቃውሞ አያያዝና አመራር፤

3.1.1.4. ለድልድል የወጡ ደንቦች አፈፃፀም ሁኔታ፤

3.1.1.5. የቢሮዎች አደረጃጀትና የሎጅስቲክ አሞላል፤

3.1.1.6. የሥራ ግንኙነት፣ ፍሰት እና የህጎች አተገባበር፤

3.1.1.7. የተገኙ አዳዲስ ተቋማዊ ባህልና አስተሳሰቦች፣ አጠቃላይ የለውጥ ውጤቶች፤

I. የገጠር ወረዳና ቀበሌ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ አፈፃፀም በተመለከተ፤

3. በገጠር ወረዳና ቀበሌ ስለተሠሩ የልማት ሥራዎችና ዴሞክራሲያዊ አሰራሮች በተመለከተ የተደረገ መከታተል፤

3.1. ሕዝቡን አሳምኖ የልማት ዕቅዶችን በቅንጅት ከማስፈፀም አንጻር የተዘረጋ አሠራርና የአደረጃጀት ስርዓት፤

3.2. ስለ ሞዴል ግለሰብና መንደር አመራረጥና ለልማት ሥራ የሰጠው አስተዋፅዖ፤

3.3. የሕ/ሰቡን ጥያቄ ተቀብሎ ቶሎ ምላሽ ከመስጠት አንፃር የተሰሩ ስራዎች፤

3.4. የግልፀኝነትና የተጠያቂነትን አሠራር በተከተለ የተሠሩ ሥራዎች፤

3.5. የፍትሀዊነት፣ የህግ የበላይነት፣ ቀልጣፋነትና ውጤታማነት ለመታየቱ የተደረገ መከታተል፤

VI. የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ እንቅስቃሴን በተመለከተ፤

3.6. የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ አመራረጥ ሚናና የታዩ ውጤቶች፤

III. የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም በተመለከተ፤

## የተፈፀሙ ዝርዝር ቁልፍ ተግባራት

1. እያንዳንዱ መሠረታዊ የአሠራር ሂደት ለውጡን (BPR) የሚተገብሩ ሴክተርና ወደ ሙሉ ትግበራ ከመገባቱ በፊት በትግበራ ወቅት የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ማለት የድልድል ኮሚቴ በመመሪያው መሠረት መቋቋም፣ አፈፃፀሙን መከታተልና ድጋፍ መስጠት፣ የግንኙነት ሥርዓት የለውጥ አመራር ስትራቴጂ እንዲሁም የክትትል፣ የግምገማና ግበረ መልስ ሥርዓት የያዘ መርሃ ግብር አዘጋጅተው እየሠሩበት እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡
2. የሙሉ ትግበራውን ሥራ ለመጀመር በ06/04/2001 ዓ/ም የድልድል ኮሚቴ በማስፈፀሚያ ደንብ 72/2001 ዓ/ም መሠረት በመቋቋም ኮሚቴው የሙሉ ትግበራውን ሥራ በማስፈፀሚያ ደንቡ መሰረት ለማከናወን በ10/4/2001 ዓ.ም

እና በ18/4/2001 ዓ/ም በድልድል መመሪያ ላይ የጋራ ግንዛቤ ፈጥሮ ወደ ሥራው ለመግባት በመመሪያው ላይ ውይይት መደረጉ፤

- በ14/10/2001 ዓ/ም የእያንዳንዱን ሠራተኛ ማህደር በማጣራት በድልድል መመሪያው መሠረት የማደራጀት ሥራ መሠራቱ፤
- በ15/4/2001 ዓ/ም በየሥራ ሂደቱ ያመለከቱ ሠራተኞች የማወዳደር ሥራ በማካሄድ ሠርቶ ከጨረሰ በኋላ ከ22/4/2001 ዓ/ም ጀምሮ ሠራተኛው የተመደበበትን የሥራ ሂደት አውቆ እንዲያከናውኑ የምደባ ደብዳቤ እንዲደርሳቸው መደረጉና በየሥራ ሂደቱ ለተመደቡ ሠራተኞች የግንዛቤ ማስጨበጫና ለአሠራር የሚረዳ ስልጠና ከጥር 04/2001ዓ/ም እስከ ጥር 08/2001 ዓ/ም ድረስ ወስዶ በመመለስ ከጥር 12/2001 ዓ/ም ጀምሮ የሙሉ ትግበራው ሥራ ተጀምሯል፡፡

3. የእያንዳንዱ የሥራ ሂደት ባለቤት አስተባባሪና ፈጻሚዎች አንድ ላይ ሆነው ተገቢውን ግብዓት ማሰባሰቢያ ቅጽ በማዘጋጀት የሙሉ ትግበራው በትክክል እየተካሄደ እንደሚገኝ እንዲሁም የድርጊት መርሀ-ግብር መሠረት ስለመጠናቀቁ ቼክ ሊስት አዘጋጅቶ ክትትል ግምገማ በማድረግ የሥራውን እንቅስቃሴ በመከታተል እየተመራ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡
5. ቀደም ሲል በተላለፈው የሠራተኞች ድልድል ማስፈፀሚያ ደንብ መሰረት የሠራተኞች ድልድል ተካሂዶ በድልድሉ የተካተቱ ሰራተኞች ሥልጠና ወስደው ከተመለሱ በኋላ ስላልተደለደሉ ሠራተኞች ጉዳይ በሚወጡ ተጨማሪ የማሻሻያ መመሪያዎች መሠረት ምደባ የተሰጣቸው ሠራተኞች እና በአንዳንድ የሥራ ሂደቶች ላይ የሰው ሀብት በድልድልና በቅጥር ተሟልቶ ባለመገኘቱ ሥራው መቆም ስለሌለበት ባለው ሠራተኛ ሥራው እየተካሄደ በመሆኑ ስልጠና ሳይወስዱ የተካተቱ ሠራተኞች መኖር የግድ ሆኗል፡፡
6. በሴክተሩ የለውጥ ተቃውሞ አያያዝና አመራር ስልቱ በቅድሚያ መሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ የሙሉ ትግበራ ስትራቴጂና የሠራተኞችን ድልድል ለማስፈፀም የወጣ ደንብ ቁጥር 72/2001 መመሪያዎች ላይ አጠቃላይ የጽ/ቤቱ ሠራተኞች ግንዛቤ እንዲጨብጡ ከመደረጉም በላይ የጽ/ቤቱ ማኔጅመንት ጠለቅ ያለ ዕውቀት ኖረውት ለመምራት እንዲችል ተከታታይ የሆነ ውይይትና መረዳዳት በማድረግ ሊነሱ የሚችለውን የለውጥ ተቃውሞ ለመያዝ በቅድሚያ የተነደፈ ስልት ሲሆን ቀጥሎም የትግበራውን ሂደት ለመከታተል ቼክ ሊስት አዘጋጅቶ በመከታተል ድጋፍ መስጠት፣ ለተፈጠሩ ችግሮች መፍትሄ በመስጠት በአመለካከት፣ በአስተሳሰብና ለውጡን በመደገፍ ተተኪ የለውጥ ኃይል ሊሆኑ የሚችሉትን የማፍራት ሥራ በየደረጃው እየተሠራ ይገኛል፡፡
7. የሥራ ሂደት አስተባባሪዎች አመዳደብ በማስፈፀሚያ ደንብ ቁጥር 72/2001 አንቀጽ 10 ን/አንቀጽ 2 ሥራ በተ.ቁ.5 ላይ በሚገልፀው መሠረት በየሴክተሩ ኃላፊ ብቃት ያላቸው ዕጩዎችን በመመልመል የአስተዳደር ምክር ቤት አቅርበው ምክር ቤቱም የያንዳንዱ ዕጩ የመፈፀምና የማስፈፀም ብቃት ከገመገመ በኋላ ሹመቱን አጽድቆ እንደሚሰጥና ሌላው በአመራሩና በሠራተኞች ዘንድ ታማኝ መሆኑ የተመሰከረለትና በሥራ ሂደቱ የተመለከተውን ዝቅተኛ ተፈላጊ ችሎታ የሚያሟላ ፈፃሚ ተመርጦ ምደባ በመስጠት የሥራ ሂደቱን እየመሩ የሚገኙ ሲሆን በአንዳንድ መ/ቤቶች ግን በግንዛቤ ማነስ ምክኒያት የሥራ ሂደት አስተባባሪዎች ምደባ በማስፈፀሚያ ደንቡ ላይ ከሚገለፀው ውጭ በመሆኑ ማስተካከያ እንዲደረግ የተሠራ ሲሆን በእያንዳንዱ መ/ቤቶች ደግሞ የሥራ ሂደት አስተባባሪ ሆኖ ምደባ ይሰጠኝ

የሚል ጥያቄዎች ይነሱ የነበረበት እንዳለም ታውቆ ማስተካከያ እንዲወሰድና የነበረው የግንዛቤ ማነስ ችግርም እንዲታረም የማድረግ ሥራ ተሠርቷል፡፡

8. በድልድሉ ደንብ ላይ የተዘረዘሩትን የድልድል መስፈርቶች መሠረት በማድረግ የሠራተኞች ምደባ በግልፅ ውድድር የተፈፀመ ሲሆን በሌሎች መ/ቤቶች የተሠራው ድልድል የተላለፈውን የማስፈፀሚያ ደንብ በተከተለ የተሠራ ለመሆኑ በማጣራት የማስተካከያ ድጋፍ ከመስጠቱም በተጨማሪ የወረዳው የመፍትሄ አማራጮች አስተግባሪ ግብረ ኃይል ሰብሳቢ እንደመሆኑ መጠን በመ/ቤታችን ያልተመደቡ ነገር ግን በሌሎች መ/ቤቶች ሊያሟሉ በሚችሉበት ቦታ ላይ ሊመደቡ የሚችሉ የ47 ሠራተኞች ምደባ ተሰጥቷል፡፡

9. በሰው ኃይል አመዳደብ ላይ የታዩ ክፍተቶች መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥን በሚተገብሩ መ/ቤቶች ያለው መዋቅር ሙሉ በሙሉ ተጠንቶ ያለመለቀቅ በአንዳንድ መ/ቤቶች በመ/ቤቱ የሚተገበረው ዋናው የሥራ ሂደት እያለ ደጋፊው የሥራ ሂደት መቅደም በመጀመሪያ ዙር ሙሉ ትግበራው ውስጥ የተካተቱ መ/ቤቶች መዋቅር ሙሉ በሙሉ አለመለቀቅ (ለአብነት ጤና ጥበቃ) የአንዳንድ መ/ቤቶች መዋቅር እስከ ዝቅተኛው የትም/ት ደረጃ ድጋፍ ሰጪ ድረስ የሚጋብዝ ሆኖ ሲፈቀድ የሌሎች መ/ቤቶች ከዲፕሎማ በላይ የባለሙያ መደብ ሆኖ መፈቀዱ ወዘተ... በየመ/ቤቶች እየተሠራ ያለው ሥራ በአዲስና በአሮጌ ተቀላቅሎ እንዲሠራ ከማድረጉም በተጨማሪ የሚሠሩ ሠራተኞችም በሁለት መልክ የሚገኙ በአዲሱ ስልጠና ወስዶ የሚሠሩና በበፊቱ በነበሩ አስተሳሰብ የሚሠሩ ሆኖ መገኘቱ ጽ/ቤቱ ድጋፋዊ ክትትል ለማድረግ ሲሄድ የሚነሳ ጥያቄና በተጨባጭ የታየ ክፍተት መሆኑና ለእነሱ ጥያቄዎችም በቂና እውቀት የተሟላ ምላሽ ለመስጠት እንደችግር መታየቱ፡፡

10. የሥራ ሂደቱና በውስጡ የያዛቸው ሠራተኞች ተገቢነት በተመለከተ በትግበራ ስትራቴጂ፣ በማስፈፀሚያ ደንብ ቁጥር 72/2001 ዓ/ም እና ቀጥሎ በወጡ የማሻሻያና ተጨማሪ መመሪያዎች መሠረት የተከናወነ ስለሆነ ችግር አልታየም፡፡

11.በሥራ ሂደቱ ላይ ተወዳድረው ሰያልፉ ወይም ግልፅ ባልሆነ ሁኔታ በውድድር ካሸነፉት ሠራተኞች ጋር የተቀላቀሉ ሠራተኞች ስለመኖራቸው ለሚለው ግልፅ ባልሆነ ሁኔታ የተቀላቀሉ ባይኖሩም በተ.ቁ.9 እና በተ.ቁ.5 ላይ በተጠቀሰው ምክኒያት የተቀላቀሉ ይኖራሉ፡፡

12. በደረጃው ያለው የድልድል ኮሚቴው አወቃቀርና ስብጥር የድልድል ደንብን በተከተለ የተዋቀረና ደንቡን ባልጠበቀ የተቋቋመ ስለመሆኑ የቀረበበት አቤቱታና ቅሬታ እንዲሁም የአሠራር ችግር የፈጠረ ለመሆኑ የቀረበበት ቅሬታ ያለመኖሩ ተውቋል፡፡

13. በድልድል የታቀፉ ሠራተኞች አዲሱ የሥራ ምደባ ደብዳቤ ላይ የተመደቡበት የሥራ መደብ መጠሪያና ቀደም ሲል ይከፈላቸው የነበረ የወር ደመወዝ መጠን የሠራተኞችን ድልድል ለማስፈፀም በወጣው ደንብ ቁጥር 72/2001 ጥናት ሰነድ ውስጥ በሚገልፀው መሠረት መመሪያው ተጠብቆ የተሰጣቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

14. በድልድሉ በአጠቃላይ ለልዩ ወረዳው 554 የሥራ ሂደት የተፈቀደ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 335 በሰው ሀብት ሲሸፈን 219 ክፍት መደብ እንደሆነና በአጠቃላይ ቀርበው ከተወዳደሩት 378 መካከል 335 በድልድሉ ሲታቀፉ 43 በድልድሉ ያልታቀፉ መሆናቸው ታውቆ ሪፖርት ተደርጓል፡፡

15.በምደባ ካልታቀፉት 43ቱ 50% እናበላይ የተሰጣቸው መሆኑን ከየመ/ቤቶች የተላለፈው ማስረጃ ያመለክታል፡፡

16.በየሥራ ሂደቶቹ የቢሮዎች ዝግጅትና አቀማመጥ ለሥራው ያለው ምቹነት በተመለከተ አሠራሩም ሆነ አደረጃጀቱ አዲስ እንደመሆኑ መጠን ሥራው ሲጀመር የተወሰነ ክፍተት ታይቶ የነበረው ቢሆንም በሂደት የሥራ ክፍሎችና የመገልገያ ቁሳቁሶች እንዲሁም የቢሮዎች ዝግጅትና አቀማመጥ ለሥራው ምቹ በሆነ ሁኔታ እየተስተካከለ በመሄዱ የትግበራው ሥራ በታቀደለት እየተመራ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

17.. ትገበራውን የተሳካ ለማድረግ ለየሥራ ሂደቶቹ የሚያስፈልጉና በሴክተሩ በኩል የተደረገ የቁሳቁሶችና መሳሪያዎችአቅርቦትና አደረጃጀት በተመለከተ በሁሉም ጋ የቁሳቁሶችና መሳሪያዎች ያለ በመሆኑ በጎላ መልኩ የተደረገ የለም፡፡

18. የሥራ ሂደቶቹ የተጠኑትና የሚተገበሩት በሴክተር ደረጃ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ሴክተሮች ለየሥራ ሂደቶቹ ያደረጉት የበጀትና የማቴሪያል ድጋፍ የለም፡፡

19. በየሥራ ሂደቶቹ ባለቤት/አስተባባሪና/ በፈፃሚወች መካከል ያለውቅ ግንኙነት ምን እንደሚመስል በተለይም በትግበራ እየተፈጠሩ ያሉ አዳዲስ እሴቶች ማለትም የቲም ስሜት (team sprit) ተግቶና ተተካክቶ የመሣራት ልምድ፣ የአገልጋይነት ስሜት እየተፈጠረ ነው ወይ? ለሚለው ለብዙ ዓመታት ተለምዶ ከቆየው አስተሳሰብ፣ አመለካከትና ባህሪይ በአንድ ጊዜ መላቀቅ አስቸጋሪ ቢሆንም አሁን የሚታየውና እየተፈጠረ ያለው የለውጡን አስተሳሰብና አመለካከት ይዞ የተመደቡበትን የሥራ ሂደት በጋራም ሆነ በግል ኃላፊነትና ተጠያቂነት ቡድናዊ ስሜት ፈጥሮ እየተሠራ የሚገኝ ቢሆንም በሂደት ወደተፈለገው (ወደታቀደው) መስመር መጓዙ ከጅምሩ እየታየ ስለሆነ የሚበረታታነው፡፡

20. እያንዳንዱ ክልል መ/ቤት ደጋፊ የሥራ ሂደቶች ከራሱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የማጣጣሙ ሥራ በማጠናቀቅ ወደ ታችኛው እርከን ማስተላለፍ እና በየደረጃው ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ በመጀመሪያው ዙር ትግበራ ደጋፊ የሥራ ሂደቶች ተጠንተው የተላኩት ከአቅም ግንባታና ከፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ሲሆን በተለይም በፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ተጠንቶ የቀረበው የልማት ዕቅድ ዝግጅት፣ ክትትል፣ ግምገማና ግብረ-መልስሥራ ሂደት የተጠናው እንደፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ፀባይ ስለሆነ በሌሎች መ/ቤቶች በጥናት ሠነድ ውስጥ የተመለከቱትን ተግባራት መ/ቤቶች እንደየመ/ቤታቸው የሥራ ፀባይና ይዞታ ለመተግበር የሚያስቸግራቸው እንደሆነ በሥራ ሂደቱ ላይ ተመድበው የሚሠሩ ሠራተኞች ሲያቀርቡት የሰማል፡፡

21. ደጋፊ የሥራ ሂደቶችን ለመከታተል የሚያስችል አደረጃጀት አልተፈጠረም፣ ባለመፈጠሩ በተለይ የመ/ቤቱ ዋናው የሥራ ሂደት ሳይጠና ደጋፊ የሥራ ሂደቶች የተላኩላቸው መ/ቤቶች ትኩረት ሰጥተው ያለመስራትና በሥራ ሂደቱ ላይ ለተመደቡ ሠራተኞች ድጋፍ፣ ማበረታታትና ግብዓት ያለመሟላት ችግር

መኖሩን ያወሱታልና አደረጃጀቱ ቢጠናከር ጥሩ እንደሆነ አስተያየታችንን እናቀርባለን፡፡

22. የጥናት ሠነዱ ውድቅ ያደረጋቸው ሕጎችና አስተሳሰቦችን ቀርተው በአዲስ መልክ የተቀረፁ አስተሳሰቦችንና በተተኪነት የታሰቡ ሕጎች ተፈፃሚነትን በተመለከተ በልዩ ወረዳው ሙሉ በሙሉ መተግበር ተጀምሯል፡፡
23. በየደረጃው የሚገኙ አስፈፃሚ አካላት በተሠጣቸው ተግባርና ኃላፊነት መሠረት የሥራ ሂደቱን አፈፃፀም በጋራ ውይይት ክትትል ከማድረጋቸውም በተጨማሪ ቼክሊስት አዘጋጅተው በመከታተል እንደሚገመግሙና ድጋፍ እንደሚያደርጉ በሚደረገው ድጋፋዊ ክትትል ለመረዳት ተችሏል፡፡
24. በየሴክተሩ ያሉ ኃላፊዎችና የሕዝብ ግንኙነት ክፍሎች የየሴክተራቸውን የሥራ ሂደት አተገባበርና አጠቃላይ ሁኔታ መረጃዎችን ለሕዝብ ከማሳወቅ አኳያ እያከናወኑት ያለው ተግባር ምን ይመስላል ለሚለው ገና የሚሠራ ተግባር ስለሆነ በአሁኑ ደረጃ አልተሠራም፡፡
25. በእያንዳንዱ ሴክተር ውስጥ ለውጡን ሊሸከሙና ሊያራምዱ የሚችሉ የለውጥ ኃይሎች ስለመኖራቸውና መበራከታቸውን በሚመለከት መ/ቤታችን በሚያደርገው ድጋፋዊ ክትትል ከእያንዳንዱ ሴክተር ኃላፊዎችና አስተባባሪዎች ጋር ስለአተገባበሩ በሚደረገው የጋራ ውይይት ወቅት እንኳንስ በሥራ አሟልተው የተመደቡ ቀርቶ በሥራ ሂደቱም ያልተመደቡ ሠራተኞች ጭምር የተፈጠረው መሠረታዊ የአሠራር ሂደት ለውጥ የሚደግፍና ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት አስተያየታቸውን እንደሚሰጡና ከግንዛቤ ማነስ የተነሳ በተወሰኑ ሠራተኞች ዘንድ አቋምን ለይቶ ያለመሄድ ቢታይም በእነዚህ ላይ ተከታታይ የሆነ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ ቢሠራ የለውጥ ኃይል የማይሆኑበት ምክኒያት እንደሌለ መገንዘብ ተችሏል፡፡
26. የሥራ ሂደቱ አፈፃፀም ከተደራሽ ግቦች አንፃር (መጠን፣ ከጊዜ፣ ከጥራት፣ ከወጪ፣...) እየተሳካ ስለመሆኑ፣ ያልተሳካ በጥረት ተደራሽ ግብ ካለ መሠረታዊ ምክኒያቱ ለሚለው በእርግጥ የመሠረታዊ የአሠራር ሂደት ለውጡ ትግበራው ዋና ዓላማ በእነዚህ ተደራሽ ግቦች የማሳካት ጥረት ቢሆንም አሁንም በጅምር ሂደት ላይ ባለበት ማለት የሰው ሀብት በሁሉም የሥራ ሂደቶች 75% ተሟልቶ ባልተገኘበት፤ የቢሮዎች ዝግጅትና አቀማመጥ ለሥራው በአብዛኛው ምቹ ባልሆነ፤ የውስጥ አደረጃጀቱ በሚጠይቀው ሎጅስቲክ በተሟላ ባልተደራጀበት፤ በአስተሳሰብ፣ በአመለካከት፣ የባህሪይ ለውጥ ተደርጎ በሙሉ እምነት ባልተገባበት በጅምር ሂደት ላይ በመሆኑ በ4ቱም በተሟላ የታሰበ ባይሆንም በሁለትና ሦስት ተደራሽ ግቦች ስኬት እየታየ መምጣት መጀመሩን አብነቶችን በማጣቀስ መረጃ እየሰጡን ሲሆን በተጨባጭም መታየት መጀመሩ ታውቋል፡፡
27. የተገኙ አዳዲስ ተቋማዊ ባህልና አስተሳሰቦች አጠቃላይ የለውጥ ውጤቶች በተመለከተ በቲም ሥራዎችን የግልና የጋራ ኃላፊነትና ተጠያቂነት ስሜት ይዞ በመግባባትና በመወያየት ልምድ በማካፈል መስራት፤ የአገልጋይነትን ስሜት ፈጥሮ መገኘት፤ የነበረውና የተለመደው አስተሳሰብና አመለካከት በአዲሱ በለውጥ አስተሳሰብና አመለካከት በመፈጠር ለውጥን ሊሸከሙና ሊያራምዱ የሚችሉ ሰዎች ብቅ ብቅ ማለት መታየቱ በዋናነት ሊጠቀሱ የሚችሉ የለውጥ ውጤቶች ናቸው፡፡

(ii) የገጠር ወረዳና ቀበሌ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ አፈፃፀም በተመለከተ ፤

1) **{በዴሞክራሲያዊ፣ በጋራ መግባባትና በአሳታፊነት ዙሪያ}፤**

1/ ህዝቡን በግልም ሆነ በጋራ የሚያከናውናቸውን ተግባራት አምኖ ብቻ እንዲፈፅም ከማድረግ አኳያ ያለው ጥረት ምን ይመስላል? የቀበሌ መዋቅራችን በግንባር ቀደም አርሶ አደር እየተመራ ነው ወይ?

- ➢ በየጊዜው ከአመራሩ ጋር በሚደረገው ውይይት፣ በሚሠጥ ስልጠናና በመስክ ተገኝቶ በሚደረግ ድጋፋዊ ክትትል ግንዛቤ በመወሰዱ ቀደም ሲል ሲሰራበት የነበረው አስገድዶ ማሰራት ቀርቶ ሕ/ሰቡ መብቱ ተከብሮለት ግዴታውን አውቆ የሚሠራው ለራሱ ልማትና እድገት እንደሆነ በመገንዘብ መስራት እንዳለበት በአመራሩ ዘንድ ግንዛቤ በመውሰዱ አስገድዶ ማሠራት እየቀረ መምጣቱ በግንባር ቀደም አርሶ አደር እየተመራ ይገኛል፡፡

2/ ህብረተሰቡን አሳምኖ የልማት ዕቅዶችን በቅንጅት ከማስፈፀም አንፃር የተዘረጋ የአሠራርና የአደረጃጀት ሥርዓት ምንድነው?

- ➢ በቀጠናና በልማት ቡድን በመደራጀት የብዙሃን ማህበራትን በመመስረት በህዋስ ተደራጅቶ ወዘተ… በእነዚህ አደረጃጀት ህ/ሰቡን አሳምኖ የልማት ዕቅዶችን በቅንጅት የመስራት አሠራር ተዘርግቶ እየተሠራበት ይገኛል፡፡

3/ ህዝቡን አሳምኖ ወደ ልማት ለማስገባት በተግባር በማሳየት የማያቋርጥ ተሳትፎ እንዲኖርና ሞዴል በመጠቀም የማሳመን አሠራር በምን ደረጃ ይገኛል?

- ➢ አሁን ባለው የህ/ሰባችን ግንዛቤ ደረጃ ያለበትን ለይቶ ለመግለፅ አስቸጋሪ ቢሆንም የመልካም አስተዳደር መርሆችን ተግባራዊ ከማደረግ አንፃር ከወረዳ እስከ ቀበሌ አመራር ተግባራዊነት የሚያሳየው መረባረብ የሚያበረታታ በመሆኑ ዓላማው በሂደት ሙሉ በሙሉ እውን ሆኖ ይታያል ተብሎ ይገመታል፡፡

4/ ሞዴል ግለሰብና መንደር በፓኬጅ ላይ በተቀመጠው አጠቃላይና ዝርዝር መስፈርት መሰረት ለመለየትና ለመፍጠር የተደረገው ጥናትና ቅንጅታዊ

አሠራር ምን ይመስላል? /ከግብርናና ገጠር ልማት፣ ከጤና፣ ከትምህርትና ከፍትህ አስተዳደር አካላት ጋር/

- ሞዴል ግለሰብና መንደር ለመለየትና ለመፍጠር የተደረገው ጥረትና ቅንጅታዊ አሠራር በፓኬጅ ላይ የተቀመጠውን መነሻ ያደረገ ቢሆንም አንዳንድ ጉድለቶች እንደ አጠቃላይ ሲታይ አይጠፉም ተብሎ ይገመታል፡፡

4.1/ በወረዳ ደረጃ ምን ያህል ሞዴል ቀበሌ፣ መንደርና ግለሰብ በመፍጠር ተግባር ላይ ለማዋል ተችሏል?

- 1(አንድ) ሞዴል ቀበሌ፣ - መንደርና 133 ግለሰብ (ወንድ 102 ሴት31) እንዲሁም ሞዴል ወጣቶች 30 ሞዴል ህ/ሥ/ማህበራት 2 በ2001 ዓ/ም የምርት ዘመን የተመረጡ ሞዴሎች ናቸው፡፡

5/ ይህ ጥረት የልማት እንቅስቃሴያችንን ከመደገፍና ህ/ሰቡን ለልማት ሥራ ከማነሳሳት አንፃር ምን አስተዋፅዖ አድርጓል?

- የሥራ ውድድርን ለሌሎች ሞዴል ግለሰቦች፣ ቀበሌዎችና ህ/ሥ/ማህበራት ጥሩ የሆነ ለሥራ የሚያነሳሳ መንፈሳዊ ቅናት አሳድሮባቸው ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ብሎም ለሀገር ኢኮኖሚ እድገት ትልቅ አስተዋፅኦ እንደሚሰጥ ይታመናል፡፡

6/ ሞዴል በመጠቀምና ያልተቋረጠ ተሳትፎን ተግባራዊ በማድረግ በባለፉት ሦስት አመታት አመታዊ የወረዳና የቀበሌ የዕቅድ አፈፃፀማችሁ በምን ያህል ፐርሰንት እያደገ መጥቷል?________________________

7/ ሞዴል እንዴት ነው የምንጠቀመው? በሞዴል መጠቀም የተገኙ ውጤቶችን በተመለከተ አንድ ቀበሌ ከአንድ ቀበሌ፣ አንድ መንደርና አንድ መንደር ልምድ እንዲለዋወጡ ያለው የመማማሪያ መድረክ ዝግጅትና አሠራር ምን ይመስላል?

- ሞዴልን የምንጠቀመው ለምርትና ምርታማነት ማደግ የሚኖረው አስተዋፅዖ ከፍተኛ ከመሆኑ አንፃር አንድ ቀበሌ ከሌላ ቀበሌ እና አንድ መንደር ከሌላ መንደር የሚማረው መልካም ተሞክሮ ለልማት መፋጠንና የጋራ ተነሳሽነትን የሚገፋፉ ስለሆነ በተጠናከረ መሰራት እንዳለበት ይታመናል፡፡

## በጋራ መግባባትና ተሣትፎን በተመለከተ

ህዝቡን ማሳመኛ ሁለተኛው መንገድ ሁለንተናዊና ልባዊ ተሣትፎን ያረጋገጠ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት ነው፡፡

9/ ሕዝቡን በግሉና በጋራ ሥራውን ከማቀድ ጀምሮ እስከፍፃሜውና ውጤቱን እስከመገምገም የሚዘልቅ ሰፊ የሕዝብ ተሳትፎ አሠራር ከመዘርጋት አኳያ ያለው ሂደት ምን ይመስላል?

- በተለይም ከ2000 ዓ/ም ጀምሮ ሕዝቡን በግሉም ሆነ በጋራ ሥራው ከማቀድ ጀምሮ እስከ ፍፃሜው ውጤት ድረስ ያለው ሕ/ሰቡ በተሳተፈበት የመስራት ልምድ ከዓመት ወደ ዓመት እያደገ በመሄዱ ለአንድ ሀገር ሲታይም የሚሰጠው ፋይዳ ከፍተኛ በመሆኑ የሕ/ሰቡ በልማት ሥራ ላይ ያለው አመለካከት የተሻለ በማሰብ በመንቀሳቀሱ የምርት ዕድገት መጨመር ታይቷል፡፡

10/ ተሣትፎው በዋነኛነት በግል ሥራ ላይ ያተኮረ እንዲሆን /20% ለጋራና 80% ለግል ያለውን አሠራር ለመተግበር/ የተደረጉ ጥረቶች ምን ይመስላል? በተጨማሪ በጋራ ሥራ ተሳትፎን ያለማቋረጥ ለማረጋገጥና ተግባራዊ ለማድረግ ያለው አሰራር በምን ደረጃ ላይ ይገኛል?

- እያንዳንዱ ግለሰብ ለሀገር ኢኮኖሚ እድገት ከሚኖረው ድርሻ እና መንግስት የግሉን ሴክተር በማበረታታት ለልማት መፋጠን የበኩሉን ሚና እንዲጫወት ትኩረት ሰጥቶ ከሚያደርገው ድጋፍ አንፃር በግል ሥራ ላይ ያለው ትኩረት ከፍተኛ በመሆኑ የሕ/ሰቡ የኑሮ ደረጃ ከዓመት ወደ ዓመት መሻሻል እያመጣ ይገኛል፡፡ የጋራ ሥራውም ቢሆን ከማቀድ እስከ መተግበር ድረስ ያለው ሕ/ሰቡን ባሳተፈ መልኩ በመሆኑ ሊቀጥል የሚገባ እንጂ ሊቋረጥ የሚገባ ባለመሆኑ ሁለቱም ተግባራት ጎን ለጎን እየተካሄደ መሆኑ ተውቋል፡፡

11/ የተሳትፎው መድረክ በስፋት በመፍጠር ከስብሰባ ባለፈ ህዝቡ በፖለቲካዊ፣ በኢኮኖሚያዊ እና በማህበራዊ ሁኔታዎች ላይ በራሱ መድረክ ፈጥሮ ተሳታፎውን የሚገልፅበት አሠራር ተዘርግቷል ወይ? ለአብነት ይጠቀስ፡-

* በአከባቢ ዕድር ወይም (በጅጋ፣ በላጋ)፣ በደቦ፣ በማህበር፣ በህዋስ ወዘተ በእነዚህ መድረኮች ፖለቲካው፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተሳትፎውን የሚገልፅባቸው መድረኮች ናቸው፡፡

12/ በልማት ዕቅድና ውሳኔዎቸ ላይ ህዝቡን ማሳተፍ የሚያስችል አሰራር መዘርጋርት፣ የጋራ መግባባት በመፍጠርና ሁለንተናዊ ተሳትፎ የማረጋገጥ ስራ እየታሰራ ነው ወይ? ለአብነት ይጠቀስ፡-

* አዎን አሳምኖ ከማሰራት አንፃር ሕዝቡ በልማት ዕቅዶችና በውሳኔዎች ላይ እንዲሳተፍ ማድረግ ከመልካም አስተዳደር መርሆች አንዱ እንደመሆኑ መጠን ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡

13/ በእያንዳንዱ ቀበሌ አንዳንድ የእንስፔክሽን ቡድን ተቋቁሞ እየሰራ ይገኛል፡፡

14/ በተግባሮቻችን ዙሪያ በየደረጃው ያለውን ባለሙያ በብቃት ማሳተፍ የሚያስችል አሰራር መዘርጋትና ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር የተገኙ ውጤቶች ምን ይመስላሉ?

* ለተግባር ስኬታማነት በየደረጃው ያለው ባለሙያ ተሳትፎ ወሳኝና ተገቢነቱ በመታመኑ ከየትኛውም ተግባሮች በየደረጃው ያለው ባለሙያ በዕውቀት፣ በጉልበትና አስፈላጊ ሲሆን በገንዘብ የበኩሉን ድርሻ የሚከፍልበት አሰራር ተፈጥሮ እየተሰራ ይገኛል፡፡

15/ እያንዳንዱ ቀበሌ የቀበሌውን የልማት ጉዳይ፣ የፀጥታ ችግሮች፣ የማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን በቀበሌው ምክር ቤት አማካይነት በየወሩ እየተሰባሰበ ከመወያየቱም በተጨማሪ በአመት ሁለት ጊዜ ለአጠቃላይ ነዋሪው ሪፖርት በማቅረብ ህዝቡ የሚያውቅበት አሠራር ተዘረቶ እየተሠራ እንደሚገኝ ታውቋል።

## II. <u>ቶሎ ምላሽ መስጠት</u>

16. ሕዝብ በጋራ በሚያነሳቸው ጉዳዩች ቶሎ ምላሽ ለመስጠት ያለው አሠራር ምን ይመስላላል?

⇒ ሕዝቡ በየትኛውም ቦታ አገልግሎት የማግኘት መብቱ የተጠበቀለት እንደመሆኑ መጠን የሚያነሳቸው ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጣቸው ማድረግ በየደረጃው ካለ አመራር የሚጠበቅ ኃላፊነትን የሚወጣ ተግባር በመሆኑ እየተሠራበት ይገኛል።

17. ባለጉዳይን በቀጠሮ የማመላለስ አሠራር እንዳይኖር በማድረግ ባለጉዳይ ሳይጉላላ ፈጥኖ ምላሽ የሚሰጥበት ያለው አሠራር ምን ይመስላል?

⇒ በየደረጃው ለሕዝብ አገልግሎት የሚሰጥ መ/ቤት ባለጉዳይ በቀጠሮ እንዳይ መላለስ በመሥራቱ የሚሰጠውን የአገልግሎት አይነት በማሳወቅ ባለጉዳይ አገልግሎት ፈልጎ ሲመጣ ማሟላት የሚገባቸውን መረጃዎች በማሳወቅ ተገልጋዩ እስካለበት ድረስ በመሄድ እንዲሁም ከተገልጋዩ የሚሰጠውን አስተያየት በመቀበል አገልግሎት የመስጠቱን ተግባር በተፋጠነ አሠራር እንዲከተል እየተደረገ ይገኛል፡፡

18. በትክክልም ሆነ በስህተት ቅሬታ ያደረበት ዜጋ ወዲያውኑ ቅታውን የሚያሰማበት ሥርዓት የተዘረጋ ባይሆንም ማንኛውም ዜጋ በተሰጠው አገልግሎት ቅሬታ ከተሰማው በማንኛውም ጊዜ በየትኛውም ቦታ ቅሬታውን የማሰማት ሙሉ መብት አለው፡፡

19. በማንኛውም ምክንያት አጉል ተስፋ በመስጠት ዜጋውን በማይፈፅምለት ጉዳይ እንዳይመላለስና እንዳይጉላላ የተደረጉ መሻሻሎችና ጥረቶች አመራሩ አጉል ተስፋ መስጠትን ነውር መሆኑን ተገንዝቦ እየሠራ ነው ወይ?

⇒ አዎን አጉል ተስፋ መስጠት ዜጋን ከማታለል ያልተቆጠበ ተግባር በመሆኑ ትክክለኛውን ምላሽ በሕ/ሰቡ ዘንድም ተቀባይነት ማግኘትና ታማኝነተን የሚፈጥር ሲለሆነ አይሠራበትም፡፡

## III. <u>የግልፀኝነትና የተጠያቅነት አሠራር</u>

20. በውሳኔ አሰጣጥ የዕቅድ አፈፃፀም እንዲሁም ሕግ፣መመሪያና አሠራርን በተመለከተ ለሕዝብ የማሳወቅና ግልፅ የማድረግ አሠራር ዳብሯል ወይ?

⇒ አዎን ሕዝብ የማያውቀው ተደብቆ የሚሠራ ነገር የለም

21. ሕዝቡ በመደበኛ ፕሮግራም የዕቅድ አፈጻፀምን እንዲገመግም ይደረጋል ወይ?

⇒ አሠራሩ ገና አዲስ እየቀጠለ የሚሄድ ተግባር እንደመሆኑ መጠን ትኩረት ተሰጥቶ ባይሠራበትም ለወደፊት መሠራት እንዳለበት ይታመናል፡፡

22. ለግልፀኝነትና ለተጠያቅነት አመች የሆኑ አሠራሮችን ለመዘርጋት የተደረገው ጥራት ምን ይመስላል?

⇒ በወረዳ ደረጃ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ መቋቋም፣በየጽ/ቤቶች የአስተያየት መስጫ መዝገብና የሀሳብ መስጫ ሳጥን መቋቋም፣

- መ/ቤቶች የሚሰጧቸውን የአገልግሎት ዓነቶች ተገልጋይ እንዲያውቅ የማድረግ ተግባር መኖሩና አንዳንድ መ/ቤቶች እንደ መ/ቤቱ የሥራ ፀባይ ወደ ተገልጋይ ዘንድ በመሄድ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረጉ ለግፀኝነትና ለተጠያቅነት አመቺ አሠራሮችን ለመዘርጋት የተደረገ ጥረት መሆኑን ያመላክታል፡፡

23. ቅሬታ ያለው ቅሬታው የሚሰማበት የቅሬታ ሰሚ አካል ተቋቁሞ እየተሰራበት ይገኛል፡፡

24. ባለጉዳይ በሚሰጠው አገልግሎት ቅሬታ ካለውና በተሰጠው አገልግሎት እርካታ ካለገኘ የአስተያየት መስጫና ቅሬታውን የሚገልጽበት አሠራር ተፈጥሯል ወይ?

⇒ አዎን ከላይ በተ.ቁ 22 የተሰጠው ምላሽ ለዚህ ጥያቄ መልስ ይሆናል፡፡

25. በወረዳና በቀበሌ ደረጃ ጉዳይ ተቀባይና የመረጀ ዴስክ ተቋቁሞ ባለጉዳይ በቀላሉ አገልግሎት የሚያገኝበት ሥርዓት ለማጠናከር የተደረገው ጥረትና የተገኘው ውጤት ምን ይመስላል? ለሚለው

⇒ በቀበሌ ደረጃ ጉዳይ ተቀባይ ሆኖ እየሠራው ያለው የቀበሌው ሥራ አስክያጅ ሲሆን በወረዳ ደረጃ ካሉ 16 መ/ቤቶች 4 መ/ቤቶች የመረጃ ሲኖራቸው ሌሎች

የሌላቸው፣ ግን ጉዳይ ተቀባይ ሆኖ የሚሠራው ከመ/ቤቱ ኃላፊ ጀምሮ እስከ ታችኛው ሠራተኛ ድረስ የእገሌ ነው፤ወይም የኔ ሥራ አይደለም ሳይባል እየተሠራ እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡

## IV. ፍትሐዊነትና የሕግ የበላይነት

26. ሕ/ሰቡን በፍትሐዊነትና በሕግ የበላይነት ተጠቃሚ ለማድረግ ከሕ/ሰቡ ተደብቆ የሚሠራ ማንኛውም ተግባር ባይኖርም ቀደም ሲል ተለምዶ ለብዙ ዓመታት ሲሠራበት ከቆየው አድሏዊ አሠራር ፍፁም የፀዳ አሠራር ተፈጥሯል ብሎ ለመደምደም ግን ያስቸግራል፡፡

## V. ቀልጣፋነትና ውጤታማነት

27. የሥራ ቅልጥፍናና ውጤታማነትን ለማምጣት የተዘረጉ የአሠራር ሥርዓቶች ማለትም/ ከዕቅድ ዝግጅት ከሪፖረት አዘገጃጀትና አቀራረብ / በምን ደረጃ ይገኛሉ? ምን ውጤት አገኝቷል?

⇒ በሁሉም ሴክተር አንድ ወጥ የሆነ የአሠራር ሥርዓት እንዲፈጠር ከማድረጉም በላይ በተጨማሪ የሚሠሩ ሥራዎች ምን ዓይነትና በእንዴት እንዲሁም መቼ እንደሚሠሩ በግልፅ ግላጭ በሆነ ሊሠራ የሚችልበት መንገድ የሚያሳይ ሆኖ መገኘቱ ለአሠራር ምቹነትን ፈጥሯል፡፡

## VI. የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ እንቅስቃሴ በተመለከተ

28. የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ ከሕዝብ ተመራጮችን ወይም ከቀበሌ ካኒኔ አካላት ጋር ያለው ግንኙነትና የሥራ እንቅስቃሴ ምንም ችግር የሌለበት እንዲሁም የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ ምደባ ከተደረገ በኃላ በቀበሌ ይታይ የነበረው የአሠራር ጉድለት የሕዝብ አቤቱታ ቶሎ ከመስማት ጊዜ መስጠት በአጠቃላይ የቀበሌውን ሕዝብ ባማከለ ያለማስተናገድ ችግር ተወግዶ ሕዝቡም ሆነ በመንግሥት መዋቅር የሚሄዱ አካላት የሚፈልጉትን መረጃ በሚፈልጉበት ወቅት አግኝተው መምጣትና መገልገል ትልቅ ድርሻ ያለው ስለሆነ ሊበረታታ የሚገባ ሲሆን አንዳንድ ቀበሌዎች ግን በአመራር በኩል የሚደረግ ያመተባበርና ተፅዕኖ ለማሳደር መሞከር እንደማይጠፋ ለመገመት አያስቸግርም፡፡

29. የቀበሌው ሥራ አስኪያጅ ከት/ት፣ከጤና፣ከግብርና ባለሙያዎች ጋር በመቀናጀት የቀበሌውን ዕቅድ በመምራትና በማስፈፀም ትልቅ ሚና እየተጫወተ ይገኛል፡፡

30. በሁሉም የገጠር ቀበሌዎች የቀበሌውን ሥራ አስኪያጅ አሠልጥኖ ሥራ ለማስጀመር እንዲያስችል አስፈላጊውን ግብዓት ከማሟላት አንፃር በሁሉም የገጠር ቀበሌዎች ባይሆንም በአንዳንድ ቀበሌዎች ችግር አይኖርም ሊባል አይችልም፡፡ ምክንያቱም በምልመላ ወቅት አንዳንድ ችግር ይከሰቱ ነበር፤ሠልጥኖ ከተመደቡ በኃላ ለሥራ የሚያስፈልግ ቁሳቁስ ያለማስረከብ ሲፈልጉ ቀርበው የሚያቁትን ለማስረዳት ፍቃደኛ ያለመሆን በአጠቃላይ የመተባበር ችግር የታዩ ቢሆኑም በሂደት ግን ከበላይ አካል በሚደረግ ክትትልና ግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ ደረጃ በደረጃ ችግሩ እየተቀረፈ በመሄዱ አሁን በመንግሥት ዕቅድ መሠረት ሥራዎችን በመምራት እየተሠራ እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሏል፡፡

## የፍርድ ቤቶች ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም

1. በፍ/ቤቶች ፍርድን ቀልጣፋ ለማድረግ እንደ ፍ/ቤት 8ወር ርዝማኔ ነበር በBPR 2ወር ዝቅ ስላለ በዚያ ለመስራት ስልጠና እየሰጡ መሆኑ፤
2. የማህበራዊ ፍ/ቤቶች በተሠጣቸው ሥልጠና ሙሉ ለህብረተሰቡ አስተዋፅኦ እያበረከተ ነው ለማለት አይቻልም፤

- ያልተሟላበት አለ
- ተግባራቸውን ያቆሙ አሉ
- በከፊል የሚሠሩ አሉ

5.የተዘዋዋሪ ችሎት ችግር
- የማስቻያ ቤት ችግር፣ ቤቶች እያሉ ፈቃደኛ ያለመሆን
- ዳኞች በሚሄዱበት ወቅት የማደሪያ ችግር

9. በይግባኝ ክርክር
ከዚህ በፊት ይግባኝ የሚረጋገጠው በእጅ ስለነበር በሚፃፍበት ጊዜ በተለያዩ ምክኒያቶች የሚዘገይበት ሁኔታ ነበር አሁን ግን ፎርማት ተዘጋጅቶ በፎርማቱ ተጠቅሞ እንዲጠይቁ ስለሚደረግ ኮፒ አድርጎ ለመስጠት 5 ደቂቃ ብቻ ይፈጃል፡፡

10. የባለፈውን መሠረት በማድረግ የዘንድሮውን በማቀድ ለውስብስቡ 8ወር ለሌሎች 1ቀን በሰዓት እንዲያልቅ ይደረጋል፡፡ በወር ስንት እንደሚወሰኑ ሪፖርት ያደርጋሉ፣ በጥንካሬው ፊት የወጡ ጥንካሬው ጥሩ እንደሆነ ይገለፅለታል ወደ ኋላ የቀረው አሻሽል እየተባለ ድጋፍ ይሰጠዋል፡፡

13. የቀረበ 1755 ውሳኔ ያገኘ 1481

14. ውሳኔ ያላገኙ ጉዳዮች 274
- ምክኒያት ከግንቦት ጀምሮ እስከ ሰኔ 20 89 መዝገብ መግባቱ
- ከወረዳ ተከማችቶ 188 መዝገብ በመምጣቱ
- በምስክር አለመገኘትና ተከሳሽ ከቦታው መራቅ

17. - ቁሳቁስ እንዲሟላ ተደርጓል
- ፎርማቶችን ማዘጋጀት
- የፋይል እንቅስቀቃሴ መቆጣጠሪያ ፎርማት ማዘጋጀት ተችሏል
- የመኖሪያ ቦታ ዝግጅት ተደርጓል

<u>በልዩ ወረዳ የዐቃቤ ህግ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራም</u>

2. ከደጋፊ የሥራ ሂደት በስተቀር ዋናው የሥራ ሂደት ተጠንቶ ባለመውረዱ ወደ ትግበራ አልተገባም፡፡

3. የማስረጃ አቀራረብና ቀጠሮ መራዘም ለማስቀረት የተዘረጋ ስርዓትን አስመልክቶ ወደ ሙሉ ትግበራ ባለመገባቱ ለውጥ የለም፡፡

5. የውልና ማስረጃ ላይ እና የማህበራት ምዝገባ ላይ ቅድመ ሁኔታ ተዘጋጅቶ በዚያ መጠቀም እንዲቻል ግልፅ በሆነ ቦታ ተለጥፏል፡፡

6. ዘመናዊ አይደለም ፡- ምክኒያት ቴክኖሎጂን መጠቀም ያለመቻልና የቁሳቁስ ችግር፡፡

7. የሕግ ንቃት ትምህርት የተሠጣቸው ለ3000 የሕ/ሰብ ክፍሎች ለመስጠት ታቅዶ ለ62 ወንድ 652 ሴት ድምር 714 ተሰጥቷል፡፡

8. ለወንጀል ሰለባ ለሆኑና ጥቆማ አቅራቢዎች የደህንነት ጥበቃ እንዴት መተግበር እንዳለበት ግልፅ ባለመሆኑ አልተደረገም፡፡

9.ለወንጀል ክስ ማስረጃ አቅራቢዎች ወይም ምስክሮች የተመደበ ገንዘብ 15000 ሲሆን ሥራ ላይ የዋለው 6205.00 ነው፡፡

10.በሃሠት መስካሪነት በህግ ተጠያቂ ከማድረግ አንፃር 15 መዝገብ ቀርቦ 14 ውሳኔ አግኝቷል፣ የሰዎቹም ብዛት 25 ነው፡፡

11. ፍትህን በፍጥነት አቀላጥፎ ለመስጠት እንዲቻል የሰው ኃይል በበቂ ተሟልቷል፡፡

12. ከደጋፊ የሥራ ሂደት በስተቀር ተጠንቶ ለመውረድ በመዘግየቱ ወደ ሙሉ ትግበራ አልተገባም፡፡

## የልዩ ወረዳ ም/ቤት ዕቅድ ክትትልና ግምገማ

1. የዕቅድ ክንውን ለመገምገም የተደረገ ክትትልና ግምገማ ሳይሆን በወረዳው ላይ በነበረው ያለመረጋጋት መክንያት ዕቅድ ለማፅደቅ 1 ጊዜ ጉባኤ ተደርጓል።
2. የምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ በተመረጡ መ/ቤቶች የፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች በመስክ የተደረገ ግምገማና የተሰጠ ግብረ-መልስ በ3 መ/ቤቶች ተደርጓል።
3. የወጡ አዋጆችን በተመለከተ ሕገ-መንግሥቱ ለወረዳ ምክር ቤት አባላት፣ለቋሚ ኮሚቴዎች፣ለት/ቤቶች እንዲሁም ለሁሉም ቀበሌዎች እንዲደርሳቸውና ግንዛቤ እንዲፈጥሩ ተደርጓል።
4. ለሁሉም የም/ቤት አባለትና የቋሚ ኮሚቴ የማስፈፀም አቅም ለማጎልበት ለቀበሌ ቋሚ ኮሚቴዎች የሦስቱን የመንግሥት አካላት አንድነትና ልዩነት፣ ስለመልካም አስተዳደርና የቋሚ ኮሚቴ ተግባራ አስመልክቶ/አደረጃጀትና የሥልጣን ተግባር ሥልጠና ተሰጥቷል።
   - ⇒ የቀበሌ አፈ-ጉባኤዎች ፎረም በማቋቋም እንዴት መተግበር እንዳለባቸው ሥልጠና ተሰጥቷል።
   - ⇒ ለወረዳ አመራሩ ሕገ መንሥቱ አስመልክቶ ሥልጠና ተሰጥቷል።
5. በምክር ቤቱ አፈፃፀም የአሠራር ደንብ መሠረት ለአብነት የሚጠቀሱ ሥራዎች
   - ⇒ በቀበሌ ላይ ፎረም በማቋቋም እንዲወያዩ መደረጉ ልምድ ልውውጥ እንዲያደረጉና ክፍተቶቻቸውን ለይቶ እንዲተገብሩ ጥረት እየተደረገ የሚገኝ ሲሆን ያጋጠሙ ችግሮች በተቀመጠለት ጊዜ አለመተግበርና መቆራረጥ ናቸው፡፡
6. በወጡ ረቂቂ አዋጆች አስተያየት እንዲሰጥ በተዘረጋ ሥርዓት በ2001 ዓ.ም በአንድ ረቂቂ ላይ አስተያየት ተሰጥቶበታል።
7. የBPR አተገባበርን አስመልክቶ ጥናቱ ከደጋፊ የሥራ ሂደት በስተቀር ተጠንቶ ስላልወረደ ወደ ትግበራ አልተገባም። ደጋፊ የሥራ ሂደቶች በጥናቱ መሠረት እንዳይተግብሩ የቁሳቁስ ችግር ገጥሟቸዋል።

## የልዩ ወረዳ ማረሚያ ቤቶች ማሻሽያ ንዑስ ፕሮግራም

1. የማረሚያ ቤቶች የመኖ አቅርቧት ግዥ ግልፀኝነትን የተከተለ እንዲሆን የታራሚ ኮሚቴ በማቋቋም አብሮ እንዲገዛ ተደርጓል።
2. ከBPR አተገባበር አንፃር ያጋጠመ ችግር ከሰው ኃይል ምደባ ጋር በአስተባባሪ ምደባ በት/ት ዝግጅቱም ሆነ በለሙያ መስመሩ መስፈርቱን የማያሟላ ባለሙያ መመደብና ከደንቡ ጋር ግንዛቤ ለመፍጠር ቢሞከርም ያለመተግበር ችግር ታይቷል።

## የልዩ ወረዳ ፖሊሲ ማሻሽያ ንዑስ ፕሮግራም

1. የሕ/ሰቡ ሠላምና ደህነት ለማስጠበቅ ፖሊስን የማስፈፀም አቅም ለማሳደግ የተሠጠ ሥልጠና፡-

- ለBPR የተሠጠ ሴት 4 ወንድ 54
- የወንጀል መከላከል መሠረተ ሀሳብና HIV Aids የሕፃናት የሴቶች ጥበቃና እንክብካቤ ሥልጠና ወንድ 64 ሴት 5
- ለማህበራዊ አገልግሎት ባለሙያ ወንጀል መከላከል ወንድ 10 ሴት

2. በወንጀል መከላከል በየቀበሌው ቤት ለቤት በማስተማር የመከላከል የማስጠንቀቅ ሥራ ተሠርቷል፡፡ ወንድ 7644 ሴት 3547
3. ኮሚንት ፖሊሲንግን በማጠናከርና በወንጀል መከላከሉ ሂደት በ34 ቀበሌዎች ተመሥርቷል፡፡ ለአካቢው ሕ/ሰብ ወንጀልን ለመከላከል የሰጠው አስተዋፅዖ ካለፈው ሁኔታ ጋር ሲነፃፀር ከነበረበት 85% ወደ 60% ወርዷል፡፡
4. ከዚህ በፊት ፖሊስ ወረዳ ላይ ተከማችቶ ይገኝ ከነበረበት ከየካቲት 4 ጀምሮ ወደየቀበሌ ተመድቦ ሕ/ሰብ ውስጥ ሆኖ እንዲሠራ ተደርጓል፡፡
5. የኮሚኒት ፖሊሲንግ አደረጃጀት ያልደረሰባቸው ቀበሌዎች የሉም፤
6. ከኮሚኒት ፖሊሲንግ አደረጃጀት ዉጪ የአካበቢ ፀጥታ ችግሮችን ለማስወገድ የሚሊሻና የፖሊስ ኃይል በቅንጅት ፀጥታን እንዲጠብቁ ከሚሊሻ ጽ/ቤት ጋር የማጠናከር ሥራ ተሰርቷል፡፡
7. የምርመራ ሥራ ተጠንቶ ባለመውረዱ ምክምንያት ወደ ትግበራ አልተገባም፡፡
8. ተጠርጣሪ ወንጀለኛ ከመያዙ በፊት 90% ያክሉ መረጃ በቅድሚያ ተሰብስቦ ወንጀለኛ መሆኑ ሲረጋገጥ ይያዛል፡፡
9. ከBPR አተገባበር አንፃር የተገኘ ውጤትና ያጋጠማቸው ችግር፡-

- **የተገኘ ውጤት፡-** በወንጀል መከላከል የሥራ ሂደት ለሕ/ሰቡ የሚሰው አገልግሎት ከዚህ በፊት ፖሊስ ይኖር የነበረው በተወሰነ ቦታ ስለነበረ ወንጀሉ ከተፈፀመ በኃላ ይደርስ ነበር፡፡ አሁን ግን እዚያው ሕ/ሰብ ውስጥ ሆኖ ወንጀል እንዳይከሰት መሥራት መጀመሩ ትልቅ ለውጥ አምጥቷል፡፡
- ቀደም ሲል ሕ/ሰቡ ጥቃቀን ጉዳዮች ይዞ እስከ ወረዳ ይመላለስ ነበር፡፡ አሁን ግን በሕ/ሰቡ መሀል ሆኖ ማግባባት በመቻሉ ልማታቸው ላይ ብቻ ትኩረት እንዲሰጡ ምቹ ሁኔታን ፈጥሮዋል፡፡ ሊቋረጥ የማይችል ክስ ካልሆነ በስተቀር የሚጉላላበት መንገድ የለም፡፡
- **ያጋጠሙ ችግሮች፡-** የተሟላ የሰው ኃይል እጥረት፣የፖሊስ አባል በየቀበሌ እንዲኖር ሲደረግ የመኖርያ ቤት እጥረት፣የውስጥ ድርጅቱ በጥናቱ መሠረት ያለመሟላት/የቁሳቁስ ችግር/ የበጀት እጥረት፣በሰው ሀብት ሥራ አመራር የሥራ ሂደት ላይ ሲቪል አይመደብም፣ ከክልል ሲቪል በመባሉ ምክንያት ት/ት ዝግጅቱና የሙያ መስመሩ የማይጋብዘው ባለሙያ መመደቡ፣በዕቀድ ዝግጀት ክትትል ግምገማ ግብረ መልስ የሥራ ሂደት ላይ እንደዚሁ ከመስፈርቱ ውጪ የተደረገ ምደባ፣መረጃ ኦፊሰር ላይ የአንድ ዓመት ሥራ አመራር ሥልጠና የወሰደ ባለሙያ ምደባ ተደርጓል፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው በፖሊስ ጽ/ቤት አባሉ መስፈረቱን ማሟላት ባለመቻሉ ምደባ የተሰጠ በመሆኑ በደንቡ መሠረት ለማስኬድ ችግር ገጥሟል፡፡